| | |
|---|---|
| ዘፍ፡22:1-19<br>1. ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፤ እንዲህም አለው፡- አብርሃም ሆይ፡፡<br>2. አብርሃምም፡- እነሆ አለሁ አለ፡፡ የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሀቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ፤ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለ፡፡<br>3. አብርሃምም በማለዳ ተነሥቶ አህያውን ጫነ ሁለቱንም ሎሌዎቹንና ልጁን ይሥሐቅን ከእርሱ ጋር ወሰደ እንጨትንም ለመሥዋዕት ሰነጠቀ፤ ተነሥቶም እግዚአብሔር ወዳለው ቦታ ሄደ፡፡<br>4. በሦስተኛውም ቀን አብርሃም ዓይኑን አነሣና<br>5. ቦታውን ከሩቅ አየ፡፡ አብርሃምም ሎሌዎቹን አላቸው፡- አህያውን ይዛችሁ ከዚህ ቆዩ፤ እኔና ልጄ ወደዚያ ሄደን እንሰግዳለን፤ወደ እናንተም<br>6. እንመለሳለን፡፡ አብርሃምም የመሰዋዕቱን እንጨት አንሥቶ ለልጁ ለይስሐቅ አሸከመው፤ እርሱም እሳቱንና ቢላዋውን በእጁ ያዘ ሁለቱም አብረው<br>7. ሄዱ፡፡ ይስሐቅም አባቱን አብርሃምን ተናገረው፡- አባቴ ሆይ አለ፡፡ እርሱም፡- እነሆኝ ልጄ አለው፡፡ እሳቱና እንጨቱ ይኸው አለ፤የመሥዋእቱ በግ<br>8. ግን ወዴት ነው? አለ፡፡ አብርሃምም፡- ልጄ ሆይ የመስዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል አለው፤ ሁለቱም አብረው ሄዱ፡፡<br>9. እግዚአብሔር ወዳለውም ቦታ ደረሱ፤ አብርሃምም በዚያ መሠውያውን ሠራ፤ እንጨትንም ረበረበ፤ ልጁን ይሥሐቅንም አስሮ በመሠውያው በእንቸቱ<br>10. ላይ አጋደመው፡፡ አብርሃምም እጁን ዘረጋ፤<br>11. ልጁንም ያርድ ዘንድ ቢላዋ አነሣ፡፡ የእግዚአብሄር መልአክም ከሰማይ ጠራና፡- አብርሃም አብርሃም<br>12. አለው፤ እርሱም፡- እነሆኝ አለ፡፡ እርሱም፡- በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ አንዳችም አታድርግበት፤ አንድ ልጅህ ለእኔ አልከለከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ ሆንህ አሁን<br>13. አውቄኣለሁ አለ፡፡ አብርሃምም አይኑን አነሣ፡፡ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ፤ አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው በልጁም ፋንታ መሥዋዕት አድርጎ<br>14. ሰዋው፡፡ አብርሃምም ያንን ቦታ ያህዌ ይርኤ ብሎ ጠራው፡፡ እስከ ዛሬም ድረስ በእግዚአብሔር<br>15. ተራራ ይታያል ይባላል፡፡ የእግዘአብሔር መልአክም አብርሃምን ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ<br>16. ጠራው፤እንዲህም አለው፡- እግዚአብሔር በራሴ | <u>**አምልኮ**</u><br><br><br><br><br><br><br><br><br><br><br><br><br><br><br><br><br><br><br><br><br>ቁ.8 **የሚቃጠል መስዋዕት**<br><br><br><br><br><br><br><br><br>ቁ.12 **ፍርሃት** |

| | |
|---|---|
| ማልሁ ይላል፤ ይህን ነገር አድርገሃልና አንድ<br>17. ልጅህንም አልከለከልህምና በእውነት በረከትን<br>እባርክሃለሁ ዘርህንም እንደ ሰማ ከዋክብትና<br>በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ ፤ ዘርህም<br>18. የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል፤ የምድር አሕዛብ<br>ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ ቃሌን ሰምተሃልና።<br>19. አብርሃምም ወደ ብላቴኖች ተመለሰ ተነስተውም<br>ወደ ቤርሳቤህ አብረው ሄዱ፤ አብርሃምም<br>በቤርሳቤህ ተቀመጠ። | |